# የሼክ መሐመድ አላሙዲ ንብረት የሆኑት የሚድሮክ ደርባ እና የሳውዲ ስታር ኩባንያዎች ሁለገብ እንቅስቃሴ - በጋዜጠኛው እይታ

በሰናይት አርአያ



ሚድሮክ ደርባ ከ 2500-3000 የሚደርሱ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ከቮልቮ ኩባንያ ለመግዛት የውል ስምምነት እንደሚፈራረም ስሰማ በተባለው ሰዓት በሸራተን ሆቴል ተገኘሁ:: የተገኘሁት በመኪና ሽያጭና ግዥ የፊርማ ስነ-ሥርዓት ላይ በተመልካችነት ለመሣተፍ ቢሆንም በወቅቱ የሰማሁት ነገር ግን  እጅግ በጣም አስደንቆኛል::

የክቡር ዶክተር ሼክ መሀመድ ሁሴን አላሙዲን የግል ንብረት የሆኑት የሚድሮክ ደርባና የሳኡዲ ስታር በስሚንቶና በግብርና ምርቶች ላይ የተሠማሩት ተቋማት በልማቱ ዘርፍ የያዙትን እቅድና የተደረሰበትን ደረጃ የሚገልጽ ማብራሪያ አዳመጥኩ::

ኩባንያዎቹ የተቋቋሙት ሼኩ የሚሌኒዮሙ ታላቅ ሰው ተብለው በተሸለሙበት ወቅት የሀገሪቱን ገፅ  ለመቀየር እንደሚሠሩና በአዳዲስ የልማት መስኮች ላይ እንደሚሠማሩ ለኢትዮጵያ ህዝብ ቃል በገቡት መሰረት ነበር::

በሚሌኒየሙ በአል ወቅት ይህንን ቃል መግባታቸውን ስለማስታውስ በእርግጥ ቃላቸውን  እየተገበሩ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውንም ቁልፍ ጥያቄ ለማጣራትና ለማረጋገጥ ምቹ አጋጣሚ ስጠብቅ ቆይቻለሁ:: ሼክ መሀመድ ሁሴን አላሙዲንን ሁላችንም የምናውቃቸው በማይነጥፈው ሀብታቸውና በማይሠስተው ለጋሽ  እጃቸው ነው::



ከሁለት ሺህ አምስት መቶ እስከ ሦስት ሺህ የሚደርስ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ በአንድ ጊዜ መግዛት  እንኳን ለአንድ ግለሰብ ለአንድ መንግስትም ወገብ የሚፈትሽ ጉዳይ  እንደሚሆን ነጋሪ አያሻውም:: ይሁንና የግዥና ሽያጩ ውል ሲፈረም በአይኔ በብረቱ አየሁ:: ግን ይህ ሁሉ ከባድ መኪና ምን ያደርጋል? የትስ ያቆሙታል? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አልቀረም :: የሚድሮክ ደርባ የሥራ ሀላፊዎች የሆኑት አቶ ሀይሌ አሰግዴና አቶ ነብዩ ሳሙኤል ሰፋ ያለ ማብራሪያና መረጃዎችን ሲሰጡ ተሽከርካሪዎቹ የተገዙት ሊቆሙ እንዳልሆነና ከቅርብ ወራት በኋላ ምርት መስጠት የሚጀምረውን ሲሚንቶ ለተጠቃሚው ባለበት ያለውጣ ውረድ ለማድረስ እንዲቻል ታስቦ መሆኑን ይናገራሉ:: ሦስት ሺህ ተሽከርካሪዎች ከሲሚንቶ በተጨማሪ የሳውኡዲ ስታር የግብርና ምርት ውጤቶችንም በተቻለ ፍጥነት ወደ መሀል ሀገር ገበያና ወደውጭ ሀገራትና ወደብ ለማጓጓዝ ታስበው የተገዙ ናቸው::

እንደ ሥራ ኃላፊዎቹ ገለፃ ክቡር ዶክተር ሼክ መሀመድ በትላልቅና ሰፋፊ የልማት ሥራዎች ላይ ለመሠማራት የገቡትን ቃል በፍጥነት ወደ ተግባር በመለወጥ ከ500 ሺህ  ሄክታር መሬት በላይ ለማልማት እቅድ ነደፉ:: 80 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ለማድረግም ሰከንድ እንኳን አልፈጀባቸውም :: ወዲያውኑም በጋምቤላ ክልል ለተገኘው ሰፊ  እርሻ መሬት ልማት የሚሆኑ ከሬይስ ኢንጂነሪንግ የእርሻ መሳሪያዎችንና ማሽኖችን ለመግዛት ዶላሩን ሲመዥርጡት ለተናገሩት ቃል ምን ያህል   ታማኝ  እንደሆኑ  እናረጋግጥላቸዋለን :: የሚያስፈልጉ የእርሻ መሣሪያዎች በሙሉ ተገዙ:: ግማሹ ሀገር ቤት ገብቷል:: የተቀሩትም እየተጓጓዙ ነው:: ክቡርነታቸው ይህንን ያህል ሚሊዮን ዶላር ወጪ አድርገው በኢትዮጵያ ለማፍሰስ ያነሣሣቸው ምንድነው? ከአፋቸው ከወጣው ቃል ለመገንዘብ የሚቻለው ሀገሬንና ህዝቤን ለመጥቀምና የሃገሬን መልካም ገጽ በተቀረው አለም አስተዋውቃለሁ ብለው የገቡት ቃል ነው የሚል ነው ምላሹ::



በጋምቤላ ክልል ብቻ በዓመት 1 ሚሊዮን ቶን ሩዝ ለማምረት 250 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ እንደሚያስፈልግ ጥናቶች አረጋግጠዋል። ፌደራል መንግሥት የተፈለገውን መሬት ጥያቄ በአግባቡ ለማስተናገድ ሙሉ ዝግጅቱን አጠናቋል። ከአቶ ሀይሌ አሰግዴ ማብራሪያ ለመገንዘብ የተቻለው ሩዝን ብቻ አምርቶ ወደ አለም ገበያ በመላክ በአመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት የሚያስችል ተግባር በመፋጠን ላይ ነው:: የጋምቤላው እርሻ በሙከራ ወቅት ከፍተኛ ምርት  እንደሚሰጥ በባለሞያዎች ተረጋግጧል:: ከሌሎች ሀገሮች ምርቶች ጋር ሲነፃፀርም ከፍተኛ ጥራት ያለው ሆኖ ተገኝቷል:: አሁን የቀረው ነገር በሙከራ የተገኙትን ውጤቶች በማስፋት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሙሉ አምራችነት መሸጋገር ነው:: ለአንድ ሄክታር ሩዝ ምርት ከ 6 - 12 የሰው ኃይል ያስፈልጋል። ቁጥሩ ሲሰላ እየተለሌ ነው። ከመሀል ሀገር ብዛት ያለው ተጨማሪ የሰው ኃይል ያስፈልጋል:: ለገዙት 3ሺህ ተሽከርካሪዎች ሹፌርና ረዳቱን ጨምሮ በጥቂቱ የ6 ሺህ ሰው የሥራ ዋስትና መረጋገጡ  እልል አያስብልም? ባለ ሆቴሉ፣ ባለቡናቤቱ፣ ነዳጅ ማደያ ሠራተኛው የመንግሥት ገቢ ተቆጣጣሪው በየግሉ ሂሳቡን ያወራርደው  እኔ ብዬ ብዬ ታክቶኛል።

የሼኩ ራዕይ በዚህ ብቻ አላበቃም :: በቤንሻንጉል በአማራና በትግራይ በአፋር ክልሎችም ለስኳር ምርት፣ ለፒፒ ባግ እና ለምግብ ዘይት የሚያገልግሉ የጥሬ  ቃዎችን ለማምረት ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ ተመድቦ በሥራ ላይ በማዋል ላይ ይገኛሉ::

ፅሑፌን ስፅፍ የገንዘቡን መጠን በዶላር እንዳለ ያስቀመጥኩት የአምዱን ቦታ ለመመጠን ስለሚረዳኝ ነው:: ነገር ግን የገንዘቡን መጠን በቀላሉ ለመረዳት እያንዳንዱን ቁጥር በ13 ብር ቢያባዛ የብሩን ልኬት ያገኘዋል::

እያንዳንዱ ምርት ገና ከጅምሩ የት ገበያ ላይ እንደሚሸጥና ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያወጣ በከፍተኛ ባለሙያዎች ተጠንቶና ተረጋግጦ ተቀምጧል:: ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚመረተው ሩዝ 45% የሚሆነው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል እንደሆነ ከወዲሁ ተመላክቷል::



መቼም ይህንን ያህል የኢንቨስትመንት ሥራ ለማከናወን ከፍተኛ የሆነ ሠፊ መሬት እንደሚያስፈልገው ይታመናል ። ምናልባትም ከፍተኛ የሆነ ነዋሪ የማፈናቀል ሂደት ሊኖረው ይችላል ተብሎ ሊሠጋ ይችላል። ነገር ግን ገና ከጅምሩ ለኢንቨስትመንቱ የመረጡት ሠፋፊ መሬቶች ከአሁን በፊት ለምንም አገልግሎት ያልዋሉና ምንም አይነት ሠፋሪ የሌለባቸው እንዲሆኑ ተደርጓል ።አልፎ አልፎ ሰፋሪ ያለባቸው ቢሆንም እንኳን ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ እንደሆነ ነው።

ከሼኩ የተላለፈው  መመሪያ አቶ ሀይሌ አሰግዴ እንዳብራሩት ከይዞታው የሚፈናቀል ትንሽ ቁጥር ያለው እንኳን ቢሆን በተገቢው መካስና የልማቱ ቀዳሚ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥለት ይደርጋል ሲሉም አክለዋል። የተወሩት ነገሮች  እየተወሩ የሚቀሩ ባዶ ተስፋዎች እንዳይሆኑም እያንዳንዱ ተግባር መቼ እንደሚጠናቀቅ ግልፅ የሆነ የተቆረጠ ቀን መቀመጥ ይኖርበታል። ህዝቡም ለመከታተልና ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት እንዲችል የማሳወቅ ሀላፊነቱም የጋዜጠኞች ነውና ጥያቄው ተነሣ።

የደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ የካቲት 2011  እ.አ አቆጣጠር ምርት መስጠት ይጀምራል። ምርቱ በሚወጣበት ጊዜ ወዲያውኑ ወደ ስራ የሚሠማራ አንድ ሺህ ከባድ ተሽከርካሪ ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ በሀገር ውስጥ ገበያ ወዲያው ተፈልጎ ሊገኝ አይችልም። ለዚህም ነው ለመኪና ግዥ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው። ስለሆነም ከላይ ከተጠቀሰው ገዜ በፊት የተገዙት ሁሉም ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ለስራ ዝግጁ ያሆናሉ። በግዥ በስምምነቱም የተመለከተው ይኸው ነው።



ለእርሻው ሥራ ሙሉ  ለሙሉ መጀመር አስፈላጊ የሆነው የምንጣሮና የመሬት መደልደል የመስኖ መስመሮች ዝርጋ  ና የመሣሠሉት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በከፍተኛ ፍጥነት በመካሄድ ላይ ይገኛሉ። በተለይ የምንጣሮ ስራውን ለማፋጠን ሌሎች ኮንትራክተሮችም ተቀጥረው ተሠማርተውበታል።

ሥራውን ለማፋጠን በተለይ በጋምቤላ በምንጣሮ ዘመቻ ሥራ ላይ የተሠማሩት የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሞያዎች የመጠለያ ካምፕ እስከሚገነባ እንኳን ለመቆየት ፈቃደኛ አልሆኑም። የተያዘው  እቅድ በፍጥነት ተተግብሮ የማየት ጉጉት ስላደረባቸው በጊዜያዊ ድንኳን ተጠልለው የእለት ተእለት ተግባራቸውን እያፈጠኑ ከድህነት ለመውጣት የሚደረገውን ርብርብ ተቀላቅለዋል። እነዚህ ከ320 በላይ ሠራተኞች የሀገር ውስጥና የውጭ ተጨምረው በልማት ሥራ በከፍተኛ ተጋድሎ ላይ ያሉ ናቸው። ተጋድሏቸው ከድህነትና ከኋላቀርነት ጋር ነው። ወገኖች አትጠራጠሩ። እነዚህ ወገኖች ዛሬ በድንኳን ውስጥ ናቸው። ጥሩ የሆቴል ምግብም ላይቀርብላቸው ይችል ይሆናል። ነገር ግን ለራስ ሣይመች ወገንን ከችግር ለማውጣት ቆርጠው ወደ ጫካ መግባታቸውን  መኑ። እሪ ብለው ሸፍተዋል። ምናልባትም  እንደ ቅድመ አያቶቻቸው ድል ናፍቆዋቸዋል። ምን አለ ትሉኛላችሁ ያሸንፋሉ።

ድህነትንና ረሃብን መቀመቅ ያወርዱታል፡፡ ክቡር ሼክም አላማቸው ይሳካል፡፡ ምቀኞቻቸውና የኢትዮጵያ ጠላቶች አንገታቸውን ወደ ምድር ይደፋሉ፡፡ ለማየት ያብቃችሁ ዛሬ በበረሀማው የጋምቤላ ጫካ ያለ በቂ መጠለያ በዳስ ውስጥ ሆነው ከድህነት ጋር የተፋጠጡት የሀገር ወዳጆች የራሳቸው ጉዳይ ተብለው በዚያው አልተተውም፡፡ ዘናጭ የሆነ ለልማት የሚገባ ልዩ ዘመናዊ የመኖሪያ ካምፕ ግንባታም ጎን ለጎን በመፋጠን ላይ ይገኛል፡፡ የውጭዎቹ ባለሞያዎችም ለልማት ደጋፊ ጓዶቻቸው እውቀታቸውንና ልምዳቸውን ሊያጋሩ ቴክኖሎጂውን ወደ ኢትዮጵያ ሊያሸጋግሩ ከወገኖቻችን ጎን ተሠልፈው ከድህነት ጋር ከባድ ግብግብ ገጥመዋል፡፡



በዚህ አጋጣሚ የሥራ ኃላፊዎቹ የተናገሩትና ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነገር አለ፡፡ በቅርቡ የተመረቀው የግልገል ጊቤ ሁለት ሀይል ማመንጫ ከሚያመርተው 420 ሜጋ ዋት ሀይል ውስጥ ሚድሮክ ደርባ ብቻ 60 ሜጋ ዋት በቀጥታ ይገዛል፡፡ ልብ በሉ 60 ሜጋ ዋት ከአዲስ አበባ ከተማ ቀጥሎ በኢትዮጵያ የሚጠቀም ከተማ የለም፡፡ በአጠቃላይ ስንመለከት ጂቡቲ እንደሀገር የሚያስፈልጋት አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ፍጆ 60ሜጋ ዋት አይደርስም፡፡ ሚድሮክ ደርባ በአንድ ጊዜ ከጂቡቲ የሚመጣጠን ሀይል ይጠቀማል፡፡ ክፍያውንም ያለምንም ውጣ ውረድ በአንድ ቆጣሪ ተጠቅሞ በአንዲት ቅጠል ቼክ ይከፍላል፡፡ አስቡት ከዚህ በላይ ምን እድገት አለ? ምንም፡፡

የሚድሮክ ደርባና የሳኡዲ ስታር የንግድ ኩባንያዎች በሩዝ በሲሚንቶና በምግብ ዘይት ምርቶች ላይ ብቻ አይወሰኑም፡፡ በአለም ገበያ ተፈላጊነቱ እጅግ እየጨመረ የመጣውን የስኳር ምርትም በከፍተኛ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ለማፋጠን ታቅዷል፡፡

ሌላው ሳልጠቅስ ማለፍ የማልፈልገው ሚድሮክ ደርባ ሲሚንቶ በቀን 80 ሺህ ኩንታል ወይም 160 ሺህ ከረጢት ሲሚንቶ ያመርታል ፡፡ አስቡት በሀገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገቱን ተከትሎ ለግንባታ የሚያስፈልገው የሲሚንቶ መጠንም ቁጥር ስፍር የሌለው ነው፡፡ ይህንን ፍላጎትና ውጥረት አስተንፍሶ ሲያበቃ የተረፈውን ሲሚንቶ ወደ ውጭ የመላክና ዶላር የማፈስ እቅድም አለ፡፡ በተለይ አቶ ሀይሌ እንደሚሉት ደግሞ የሲሚንቶ ዋጋ በሀገራችን እጅግ በናረበት በአሁን ወቅትም ሆነ በሌላ ጊዜ ከአለም ዋጋ አስበልጦ ሲሚንቶን



በመሸጥ በአቋራጭ የሚገኝ ትርፍን እንደማይፈልጉ ሼክ መሀመድ አላሙዲ ከወዲሁ ግልፅ በማድረግ፣ የድርጅቱ አመራሮች በሕብረተሰቡ ላይ ምንም ዓይነት የትርፍ ጫና ሳያደርጉ ተፎካካሪ መሆን እንዳለባቸው ጠንካራ መመሪያ ሰጥተዋል፡፡

ሼክ መሀመድ አላሙዲን እድሜአቸው ይርዘምና በወንዝ ምክንያት ድልድይ አጥተው የማይገናኙ ወገኖችን ለማገናኘትም በጋምቤላ አካባቢ 132 ሜትር ርዝመት ያለው ረጅም ድልድይ በራሳቸው ወጪ

እያስገነቡ ይገኛሉ። ይህም ግንባታው በሙገር ወንዝ ላይ በመካሄድ ላይ የሚገኘው ድልድይ በመጪው የካቲት ወር ተመርቆ ለተጠቃሚው ክፍት ይሆናል ። በአንድ ግለሰብ ወጪ ይህንን ያህል ግዙፍ ድልድይ ሲገነባ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ነው። ይኼውም በቅርቡ ሲመረቅ ጋዜጠኞች በቦታው ተገኝተው እውነቱን እንደሚያዩ ከወዲህ ቃል ተገብቷል። ይህም ሳይበቃ 240 ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ አዲስ የገጠር መንገድ ግንባታ በራሳቸው ወጪ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። አቶ ነብዩ ሣሙኤል የክቡር ዶ/ር ሼክ መሀመድ ሁሴን አላሙዲ የቅርብ ረዳትና አማካሪ እንደገለፁት ደግሞ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በአማራ፣ በትግራይ፣ በቤንሻንጉል እና አፋር የሚከናወኑ እና በዕቅድ ላይ ያሉ የልማት ስራዎች በክልሉ መንግስት ከፍተኛ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግላቸው በመሆኑ ሁሉም ነገር አስቀድሞ በተያዘለት መስመርና አቅጣጫ እየተጓዘ ይገኛል። በተጨማሪም በፌደራል መንግሥት ደረጃም ከፍተኛ ድጋፍና ማበረታታት እንዳልተለያቸው በአክብሮት ገልጸዋል።



በአዲስ አበባ ከተማ ፒያሳ አካባቢ ሊሠራ ታቅዶ የግንባታ ሂደቱ የተቋረጠው ባለ 25 ፎቁ የሲቲ ሴንተር ህንፃ ፍፃሜው ምን ሊሆን ነው? የሚለው ተከታዩ የጋዜጠኞች ጥያቄ ነበር። በዚህ መሀል ለሁሉም የልማት ደጋፊ ወገን የምስራች የሆነ የድል ዜና ተበሠረ። በተሻሻለው የህንፃ ዲዛይን ሥራ ላይ ሼክ መሀመድ ሁሴን አላሙዲ ከሁለት ቀናት በፊት ባደረጉት ውይይት ከከተማው አስተዳደር ጋር ሙሉ መግባባት ላይ በመደረሱ የህንፃው ግንባ ከ15 ቀናት በኋላ በይፋ ይጀመራል። 25 ፎቆች ያሉት ይኼው ህንፃ ከሚሠጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች በተጨማሪ ለከተማዋ ውበት የሚያበረክተው አስተዋፅኦም ቀላል የሚባል አይደለም። የሆነው ሆኖ ፍቃዱ ተገኝቷል። ግንባታውም ይፋጠናል። በተመደበለት ጊዜም ተጠናቅቆ በይፋ ይመረቃል ተብሏል። ለማየት ያብቃን ብዬአለሁ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የአፍሪካ ህብረት ሆቴል ህንፃ ግንባታ ምን ደረጃ ላይ እንዳለም ማብራሪያ ተሠጥቷል። የሆቴሉ ህንፃ ዲዛይን መሻሻል ያለበት በመሆኑ እስከሚሻሻል ጥቂት የተጓተተ ቢመስልም ስራው በቅርቡ ተጀምሮ ግንባታው በመፋጠን ላይ ይገኛል ። የታገሠ ከሚስቱ ይወልዳል እንዲሉ የተያዙት እቅዶች በሙሉ በድል አድራጊነት ይፈፀማሉ። እየተፈጸሙም ይገኛሉ። የድሉ ቀንም አይዘገይም ሚድሮኮች ከአይን ይሰውራችሁ ብዬአለሁ።